በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ፍትህ ቢሮ
የህግ ምክር፣ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት

THE AMAHARA NATIONAL REGIONAL STATE
JUSTICE BUREAU
LEGAL COUNSELING, DRAFTING AND COMPILATION
DIRECTORATE

ቁጥር
Ref. No የህ/ም/ማጠ/ዳ/-1461/18
ቀን
Date 15/12/2018 ዓ.ም

ለአማራ ክልል የፍትሕና ሕግ ኢንስቲትዩት
ባህር ዳር፤

ጉዳዩ መመሪያ ምዝገባን ይመለከታል

በአማራ ክልል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 292/2017 ዓ.ም እና ማሻሻያው ላይ እንደተደነገገው ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም አዲስ መመሪያ አውጥቶ ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት መመሪያውን ከነማብራሪያው እንዲሁም አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በሥራ ላይ የነበሩ መመሪያዎችን አዋጁ በወጣ በ2 (ሁለት) ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለፍትህ ቢሮው በመላክ እንዲመዘገብ ማድረግ እንዳለበት ተደንግጓል።

በዚህ መሰረት ኢንስቲትዩቱ በቁጥር የፍ/ህ/ኢን/ልዩ/መ-18/48 በቀን 04/12/2018 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ እና የህግ ምርምር ኢንስቲትዩት የተጋባዥ ባለሙያዎች አመላመልና ክፍያ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 10/2010 ዓ.ም ምዝገባ እንዲከናወን መላኩ ይታወሳል።

ስለሆነም ፍትህ ቢሮ በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀፅ 1 በተሰጠው ስልጣን መሠረት የተላከለትን መመሪያ ቁጥር 10/2010 ዓ.ም ሕጋዊነቱን፣ መሰረታዊ መብቶችና መርሆችን የማይጥስ መሆኑን መርምሮና አስተካክሎ መመሪያው በክልል ደረጃ መመሪያ ቁጥር 154/2018 ዓ.ም ሆኖ ስራ ላይ እንዲወል የመዘገበው ስለሆነ የተመዘገበውን መመሪያ ቅጂ 09 ገጽ በዚህ ሽኜ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የላክን መሆኑን እንገልጻለን።

ከሰላምታ ጋር

የህግ ም/ማ/ማ/ዳይሬክቶሬት
ዳይሬክተር

ግልባጭ//
- ለቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት፤ (ያለ አባሪ)
- ለፍት/ሕግ ጉዳ/ዘር/ምክትል ቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት

ፍትሕ ቢሮ

Tel.No 058 222 0794/793
☎ 058 220 37 57
✉ 995
Fax- 0582221530

መመሪያ ቁጥር 154/2018 ዓ.ም

የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ እና የህግ ምርምር ኢንስቲትዩት የተጋባዥ ባለሙያዎች አመላመልና ክፍያ አፈጻጸም መመሪያ

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ እና የህግ ምርምር ኢንስቲትዩት የሚሰጣቸው የቅድመ-ስራ፣ የስራ ላይ እና የአጫጭር ጊዜ ስልጠናዎች በኢንስቲትዩቱ በቋሚነት ተሹመው ከሚሰሩ አሰልጣኝና አማካሪዎች በተጨማሪ በተጋባዥ ባለሙያዎች ታዞ የሚከናወን በመሆኑ፤

ስልጠናው በሚፈለገው መልኩና በአግባቡ እንዲሰጥ ከስልጠናው ጋር ቀጥተኛ ተያያዥነት ያላቸውን ሞጁሎችን ከፍተኛ ልምድና ብቃት ባላቸው ባለሙያዎች ለማዘጋጀትና ስልጠና ለመስጠት ወጭ የሚጠይቅ በመሆኑና የባለሙያዎችን አመላመልና የወጭ አፈጻጸም ስርዓቱን በመመሪያ መደገፍ በማስፈለጉ፤

ኢንስቲትዩቱ ከረዥም ጊዜ ስልጠና በተጨማሪ የመካከለኛና የአጫጭር ጊዜ ስልጠናዎችን በማዘጋጀት ለፍትህ አካላትና የፍትህ አካሉን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ በመደገፍ ለክልሉ ፍትህ ስርዓት ዕውን መሆን ከፍተኛ ሚና ላላቸው ተቋማት ባለሙያዎች እንዲሁም መንግስታዊና መንግስታዊ ላሆኑ ተቋማት ሰራተኞች ስልጠናዎችን ለመስጠት የሚያስችል ቅድመ-ዝግጅት በማድረግ የሚገባ በመሆኑና ለቅድመ-ዝግጅት ስራዎች የሚያስፈልገውን ወጭ መሸፈን አስፈላጊ በመሆኑ፤

የቅድመ-ስራ ስልጠናው ስርዓተ-ስልጠናው ወይም ካሪክለም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም የተዘጋጁት የስልጠና መስጫ ሞጁሎች ይህንን የጊዜም ሆነ በወቅቱ ያሉትን አዳዲስ ህጎች ወይም የሰበር ውሳኔዎች መሰረት ያላደረጉ በመሆናቸውንና ይህንን ደግሞ በየጊዜው እያጣጣሙ መጓዝ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የኢንስቲትዩቱን ክፍያ ከፈደራሉ የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ማሰልጠኛ ማዕከል እና ከሌሎች አቻ ተቋማት ካላቸው የክፍያ ስርዓት ጋር ማቀራረብ እና የክፍያ መጠኑን ከወቅቱ የገንዘብ ዋጋ ጋር በማገናዘብ ማሻሻል በማስፈለጉ የስራ አመራር ቦርዱ ስራ ላይ የነበረውን መመሪያ ቁጥር 01/2003 ዓ.ም አሻሽሎታል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ እና የህግ ምርምር ኢንስቲትዩት የተጋባዥ ባለሙያዎች አመላመልና ክፍያ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 154/2018 ዓ.ም" ተብሎ ይጠቀሳል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

1/ "ኢንስቲትዩት" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛና የህግ ምርምር ኢንስቲትዩት ማለት ነው፤

2/ "ባለሙያ" ማለት በህግ ወይም በሌሎች የትምህርት ዘርፎች ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው ሆኖ በተለያዩ ርዕሶች ሰልጣኞቹን እንዲያሰለጥን ወይም የማሰልጠኛ ሞጁሎችን እንዲያዘጋጅ፣ እንዲከልስ ወይም የአርትኦት ስራ እንዲያከናውን ኢንስቲትዩቱ የመረጠው የተፈጥሮ ሰው ማለት ነው፤

3/ "ክፍያ" ማለት ስልጠና እዲሰጥ፣ ሞጁል እንዲያዘጋጅ፣ እንዲከልስ፣ ኢዲት እንዲያደርግ በኢንስቲትዩቱ ተመርጦ ስራውን በአግባቡ ማከናወኑ ተረጋግጦ ተቀባይነት ላገኘ ባለሙያ የሚከፈል ገንዘብ ነው፤

4/ "ሞጁል" ማለት ኢንስቲትዩቱ በሚያዘጋጀው ስርዓተ-ስልጠና እና ሌሎች መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ እና በኢንስቲትዩቱ ተቀባይነት ያገኘ ደረጃውን የጠበቀ የረጅም፣ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ የስልጠና አይነቶች የሚውል የማሰልጠኛ ጽሁፍ ነው፤

5/ "የሞጁል ክለሳ" ማለት ከላይ በፊደል "ሐ" ላይ በተገለጸው አግባብና አላማ ቀደም ሲል ተዘጋጅቶ ስራ ላይ የነበረውን ሞጁል መሰረታዊ ይዘቱ ሳይለወጥ ከወቅቱ ጋር በሚሄድ መልኩ ለማዘጋጀት መቅረት ያለባቸውን የሞጁል ክፍሎች ወይም ሀሳቦች በማስቀረት እንዲሁም መጨመር የሚገባቸውን አዳዲስ ሀሳቦች ደግሞ በመጨመር የማሻሻል ስራ መስራት ነው፤

6/ "የአርትኦት ስራ" ማለት በአንድ ሌላ ባለሙያ ከላይ በፊደል "ሐ" የተዘጋጀን ወይም በፊደል "መ" የተከለሰን ሞጁል የአርትኦት ስራ መስራት ሲሆን ከቋንቋና ቃላት አጠቃቀም ትክክለኛነትን ከማረጋገጥ ጀምሮ በሞጁሉ ውስጥ እንዲካተቱ የሚፈለጉ መሰረታዊ የሆኑ ጉዳዮች በትክክል መካተታቸውን መግባት የማይገባቸው ጉዳዮች ደግሞ አለመግባታቸውን በማረጋገጥ የሚስተካከሉ ነገሮች ሲኖሩ ከሞጁል አዘጋጁ ጋር በአካል ወይም በሌላ ማናቸውም የመገናኛ መንገዶች በመገናኘት እንዲስተካከሉ ማድረግን ጨምሮ የተዘጋጀውን ወይም የተከለሰውን ሞጁል ብቁ አይደለም ብሎ ካመነ ውድቅ የማድረግ ውሳኔ መስጠትን ይጨምራል፡፡

3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ኢንስቲትዩቱ በተጋባዥ አሰልጣኝነትም ሆነ በሞጁል አዘጋጅነት፣ ከላሽነት፣ የአርትኦት ስራ እንዲሰሩ መርጦ በሚያሰራቸው ወይም በሚመድባቸው ባለሙያዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ክፍል ሁለት

ስለክፍያ መጠንና አፈጻጸም

4. የክፍያ አይነቶች

ይህ መመሪያ ተግባራዊ የሚሆንባቸው የክፍያ አይነቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1/ የፖሊሲና ስትራቴጅ ስልጠናዎችን ጨምሮ መስፈርቱን አሟልተው በኢንስቲትዩቱ በመመረጥ የቅድመ-ስራ፣ የስራ ላይም ሆነ የአጫጭር ጊዜ ስልጠና ለሚሰጡ ተጋባዥ አሰልጣኞች፤

2/ በኢንስቲትዩቱ ተመርጠው ሞጁል ለሚያዘጋጁ፣ ለሚከልሱ እንዲሁም የተዘጋጁ ወይም የተከለሱ ሞጁሎችን የአርትኦት ስራ ለሚሰሩ ባለሙያዎች እና፤

3/ ለትምህርትና ስልጠና ተጓዥ ባለሙያዎች የሚፈጸሙ የክፍያ አይነቶች ናቸው፡፡

5. የስልጠና ክፍያ መጠንና ዝርዝር አፈጻጸም

1/ የክፍያው መጠን ስልጠና የተሰጠበትን ሰዓት መሰረት በማድረግ ስራ ላይ የዋለው ሰዓት ተባዝቶ የሚከፈል ሆኖ በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጹትን

ስልጠናዎች ለመስጠት በኢንስቲትዩቱ በተጋባዥ አሰልጣኝነት ተመርጠው ስልጠና ለሚሰጡ አሰልጣኞች የሚከፈልው ገንዘብ የክፍያ አፈጻጸም እንደሚከተለው ይሆናል፦

ሀ) የመጀመሪያ ዲግሪ ላለው በሰዓት ብር 200.00 (ሁለት መቶ ብር)፤

ለ) የሁለተኛ ዲግሪ (ማስተርስ) ላለው በሰዓት ብር 220.00 (ሁለት መቶ ሀያ ብር) እንዲሁም፤

ሐ) የሶስተኛ ዲግሪ (PHD) ላለው በሰዓት ብር 250.00 (ሁለት መቶ ሀምሳ ብር) ይከፈለዋል፤

2/ በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 ከፊደል ተራ ሀ እስከ ሐ ድረስ ከተጠቀሱት የትምህርት ዝግጅቶች በተጨማሪ የረዳት ፕሮፌሰር፣ የተባባሪ ፕሮፌሰር እንዲሁም የፕሮፌሰርነት ወይም የሙሉ ፕሮፌሰርነት ማዕረግ ላላቸው ባለሙያዎች በዚሁ ድንጋጌ ከሚከፈላቸው ክፍያ በተጨማሪ በቅደም ተከተል ብር 25.00 (ሃያ አምስት ብር)፣ 50.00 ብር (ሃምሳ ብር) እንዲሁም 100.00 (አንድ መቶ) ብር በሰዓት እየታሰበ የሚከፈላቸው ይሆናል፤

3/ በዚህ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ሁለተኛ ዲግሪ ወይም ማስተርስ ኑሮት የረዳት ፕሮፌሰርነት ማዕረግ ያለው ባለሙያ የሶስተኛ ዲግሪ ወይም PHD ካለው ባለሙያ ጋር በእኩል ደረጃ ክፍያ የሚፈጸምለት ሲሆን የተባባሪ ፕሮፌሰርነትና የሙሉ ፕሮፌሰርነት ማዕረግ ላላቸው ባለሙያዎች ከላይ በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ በተገለጸው አግባብ ክፍያው የሚፈጸም ይሆናል፤

4/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ እስከ ንዑስ አንቀጽ 3 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ስልጠና የሚሰጠው ባለሙያ ኢንስቲትዩቱ ስልጠናውን ከሚሰጥበት ቦታ ውጭ ከሆነ በሌሎች መመሪያዎች አግባብ የውሎ አበል፣ የአልጋ እና የትራንስፖርት ወጭዎች የሚሸፈኑለት ይሆናል፤

5/ ኢንስቲትዩቱ በግቢ ውስጥም ሆነ ከግቢ ውጭ ወይም ሌላ ቦታ ስልጠና እንዲሰጥላቸው የሚፈልጉ ሌሎች ተቋማት ሲኖሩ ከባለሙያዎች አንጻር ተቋማቱ የራሳቸው የተሻለ መመሪያ ከሌላቸው ስልጠናውን ለሚሰጡት የኢንስቲትዩቱ አሰልጣኞች የሚከፈለው ክፍያ በዚሁ አግባብ የሚፈጸም ይሆናል፤

6/ በዚህ አንቀጽ የተገለጸው ቢኖርም እጅግ አስፈላጊ በሆኑ ስልጠናዎች ላይ ኢንስቲትዩቱ በልዩ ወይም በቁርጥ ውል ልዩ ባለሙያዎችን ጋብዞ ስልጠና ሊያሰጥ ይችላል።

6. <u>የስልጠና ሞጁል ዝግጅት፣ ክለሳ እና የአርትኦት ስራ መጠንና ዝርዝር አፈጻጸም</u>

1/ የክፍያው መጠን የተዘጋጀውን ሞጁል የገጽ ብዛት መሰረት በማድረግ ተባዝቶ የሚከፈል ሆኖ በዚህ በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለጹትን ስራዎች ለመስራት በኢንስቲትዩቱ በተጋባዥ ሞጁል አዘጋጅነት፣ ከላሽነት ወይም አርታይነት ተመርጠው ለሚሰሩ ባለሞያዎች የሚከፈልው ገንዘብ የክፍያ አፈጻጸም እንደሚከተለው ይሆናል፦

ሀ) አዲስ ለሚዘጋጅ ሞጁል በመጀመሪያ ዲግሪ ባለሙያ ሲዘጋጅ በገጽ 200.00 (ሁለት መቶ ብር)፣ በሁለተኛ ዲግሪ ባለሙያ ሲዘጋጅ በገጽ 210.00 (ሁለት መቶ አስር ብር) እንዲሁም በሶስተኛ ዲግሪ ባለሙያ ሲዘጋጅ ደግሞ በገጽ 225.00 (ሁለት መቶ ሀያ አምስት ብር)፣ ሆኖ ጠቅላላ የክፍያው መጠን ግን በቅደም-ተከተል ከብር 20,000.00 (ሀያ ሺህ ብር)፣ ከብር 21,000.00 (ሀያ አንድ ሺህ ብር) እንዲሁም ከብር 22,500.00 (ሀያ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር) ሊበልጥ አይችልም፤

ለ) ከዚህ በፊት በኢንስቲትዩቱ ተቀባይነት አግኝቶ ስራ ላይ የነበረ ሞጁል (የስልጠና ጽሁፍ) ሲከለስ በመጀመሪያ ዲግሪ ባለሙያ ሲከለስ በገጽ 100.00 (አንድ መቶ ብር)፣ በሁለተኛ ዲግሪ ባለሙያ ሲከለስ በገጽ 110.00 (አንድ መቶ አስር ብር) እንዲሁም በሶስተኛ ዲግሪ ባለሙያ ሲከለስ ደግሞ በገጽ 125.00 (አንድ መቶ ሀያ አምስት ብር)፣ ሆኖ ጠቅላላ የክፍያው መጠን ግን በቅደም-ተከተል ከብር 10,000.00 (አስር ሺህ ብር)፣ ከብር 11,000.00 (አስራ አንድ ሺህ ብር) እንዲሁም ከብር 12,500.00 (አስራ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር) ሊበልጥ አይችልም፤

ሐ) አዲስ የተዘጋጀን ወይም የተከለሰን ሞጁል የአርትኦት ስራ የሚያከናውን ባለሙያ የአርትኦት ስራው በመጀመሪያ ዲግሪ ባለሙያ ሲከናወን በገጽ 50.00

(ሀምሳ ብር)፣ በሁለተኛ ዲግሪ ባለሙያ ሲከናወን በገጽ 60.00 (ስልሳ ብር) እንዲሁም በሶስተኛ ዲግሪ ባለሙያ ሲከናወን ደግሞ በገጽ 75.00 (ሰባ አምስት ብር)፣ ሆኖ ጠቅላላ የክፍያው መጠን ግን በቅደም-ተከተል ከብር 5,000.00 (አምስት ሽህ ብር)፣ ከብር 6,000.00 (ስድስት ሽህ ብር) እንዲሁም ከብር 7,500.00 (ሰባት ሽህ አምስት መቶ ብር) ሊበልጥ አይችልም፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተገለጸው የክፍያ አፈጻጸም እንደተጠበቀ ሆኖ ለአጫጭር ጊዜ ስልጠና በአዲስ የሚዘጋጁም ሆኑ የሚከለሱ ሞጁሎች ከስልጠናው ርዕስ ስፋት አንጻር በኢንስቲትዩቱ አስፈላጊነቱ ታምኖበት 50 ገጽ እንዲደርስ ካልተፈቀደ በስተቀር ከ35 ገጽ ሊበልጥ አይችልም፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ሀ እና ለ የተገለጸው ክፍያ የሚፈጸመው የአርትኦት ስራውን የሰራው ባለሙያ ሲያረጋግጥ ሲሆን ለአርታኢው የሚከፈለው ክፍያ ደግሞ በኢንስቲትዩቱ ተረጋግጦ የሚፈጸም ይሆናል፡፡

7. <u>የፈተና ዝግጅት ክፍያ</u>

1/ በተለያዩ መንግስታዊም ሆኑ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ጠያቂነት የኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎች ፈተና በሚሰጡበት ጊዜ ፈተና እንዲሰጥለት የሚፈልገው ተቋም ብር 5,000 (አምስት ሽህ ብር) ፈተናውን አዘጋጅተው እንዲፈትን/ኑ በኢንስቲትዩቱ ለተመደበው/ቡት ባለሙያ/ዎች ክፍያ ይፈጽማል፡፡ ነገር ግን የተፈታኞች ቁጥር ከ20 የሚበልጡ ከሆነ በተጨመረው ተፈታኝ ቁጥር ብር 250 (ሁለት መቶ ሀምሳ ብር) ተጨምሮ የሚከፈል ይሆናል፤

2/ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተጠቀሰው ግንዘብ ውስጥ ፈታኝ ባለሙያው(ዎች) 50% እንዲወስድ(ዱ) ተደርጎ ቀሪውን 50% ለኢንስቲትዩቱ ገቢ የሚደረግ ይሆናል፤

3/ የፈተናው ይዘት የፈተና ጠያቂውን ተቋም ፍላጎት እንዲሁም ስልጣንና ተግባር መሰረት በማድረግ ፈተናውን አልፎ ወደ ተቋሙ የሚገባው ባለሙያ ለተቋሙ ራዕይና ተልኮ እንዲሁም ተግባርና ሀላፊነት መሳካት ከፍተኛ ድርሻ እንዲወጣ ያስችለዋል በሚል በፈታኙ ባለሙያ የታመነባቸው መሰረታዊና ስነ-ስርዓታዊ ህጎችን መነሻ በማድረግ የሚዘጋጅ ይሆናል፤

4/ የፈተናው የሚዘጋጅበት ቋንቋ እንደ ፈተናው ጠያቂ ተቋም ፍላጎት በአማረኛ ወይም በእንግሊዝኛ የሚዘጋጅ ሆኖ በተለይ የክልሉ መንግስት የስራ ቋንቋ አማረኛ ከመሆኑ አንጻር ግን ፈተና እንዲሰጥላቸው የሚጠይቁ ተቋማት ፈተናው በዚሁ ቋንቋ እንዲዘጋጅላቸው የሚኖራቸውን ፍላጎት ኢንስቲትዩቱ ያበረታታል፤

5/ የፈተናው ይዘትም ሆነ ውጤት እጅግ ሚስጥራዊ በሆነ ሁኔታ እንዲያዝ ተደርጎ ውጤቱ እጅግ ቢዘገይ ፈተናው በተሰጠ በ5 የስራ ቀናት ውስጥ ለፈተና ጠያቂው ተቋም ይሰጣል፤

6/ ይሁን እንጅ ኢንስቲትዩቱ በኮሚቴ አባልነት ለሚሰጣቸው ፈተናዎች የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት የላቸውም፡፡

ክፍል ሶስት

የተጋባዥ አሰልጣኞች እንዲሁም የሞጁል አዘጋጆች፣ ከላሾችና አርታኢዎች አመራረጥ

8. የተጋባዥ ባለሙያዎች አመራረጥ መስፈርቶች

በኢንስቲትዩቱ ጋባዥነት እንዲያሰለጥኑ፣ ሞጁል እንዲዘጋጁ፣ እንዲከልሱ ወይም የአርትኦት ስራ እንዲሰሩ የሚመረጡት ተጋባዥ ባለሙያዎች ቀጥሎ በተዘረዘሩት ሁኔታዎችና እንደ አስፈላጊነቱ ኢንስቲትዩቱ በሚያዘጋጃቸው ተጨማሪ መስፈርቶች ተመዝነው የሚለዩ ይሆናል፦

1/ በትምህርት ዝግጅታቸው ሆኖ በልዩ ሁኔታ ለሚሰጠው ስልጠና እንዲሁም ለሚዘጋጀው፣ ለሚከለሰው ወይም የአርትኦት ስራ ለሚከናወንበት ሞጁል ያለው የትምህርት ዝግጅት ወይም ቅርበት እንደተጠበቀ ሆኖ ቅድሚያ ከፍተኛ የትምህርት ዝግጅት ላላቸው ባለሙያዎች የሚሰጥ ይሆናል፤

2/ በስራ ልምዳቸውና ባላቸው ወቅታዊ የስራ አፈጻጸም ውጤታቸው፤

3/ በየኑቨርስቲ ቆይታቸው ባስመዘገቡት ውጤት፤

4/ ከኢንስቲትዩቱ ጋር ተባብሮ ለመስራት ባላቸው ተነሳሽነትና ዝግጁነት፤

5/ ቀደም ሲል በማሰልጠን፣ ሞጁል በማዘጋጀት፣ በመከለስና የአርትኦት ስራ በመስራት ባላቸው ልምድ፤

6/ በኢንስቲትዩቱ የበላይ አመራሮች፣ አሰልጣኝና ተመራማሪዎች እንዲሁም በሰልጣኞች የሚጣቸውን የግምገማ አስተያየቶች ተቀብለው ለማስተካከል ወይም ለማሻሻል ያላቸውን ሙሉ ፍላጎትና ዝግጁነት በማረጋገጥ የሚለዩ ሲሆን፣

7/ የፖሊሲና ስትራቴጅ አሰልጣኝ ሆነው የሚመደቡት የህግና የፖለቲካ አመራሮች ከላይ የተዘረዘሩት ቅድመ-ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው አመራሮችን የሚመድበው አካል በሚያወጣቸው ተጨማሪ መስፈርቶች ጭምር የሚመረጡ ይሆናል።

9. ተጋባዥ ባለሙያዎች ሊገኙባቸው ይችላሉ ተብለው የሚታሰቡ አካላት

1/ የፌደራልና የክልል የፍትህና የጸጥታ ተቋማት፣

2/ ዩንቨርስቲዎች፣

3/ የጠበቆች ማህበራት፣

4/ የአመራር ማሰልጠኛ ተቋማት እንዲሁም፤

5/ እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች ቢሮዎች እና ተቋማት ሊሆኑ ይችላሉ።

ክፍል አራት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

10. መመሪያውን የማሻሻል ስልጣን

የኢንስቲትዩቱ የስራ አመራር ቦርድ እንደ አስፈላጊነቱ ይህን መመሪያ በማንኛውም ጊዜ የማሻሻል ወይም በአዲስ መመሪያ የመተካት ስልጣን አለው፡፡

11. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው መመሪያዎች

ይህ መመሪያ በሸፈናቸው ጉዳዮች ላይ ከዚህ መመሪያ ጋር ሚቃረኑ ማናቸውም መመሪያዎች ወይም ውሳኔዎች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

12. የተሻሩ መመሪያዎች

ይህ መመሪያ ከመጽናቱ በፊት ስራ ላይ የነበረው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ እና የህግ ምርምር ኢንስቲትዩት የተጋባኙ ባለሙያዎች አመላመልና ክፍያ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 1/2003 ዓ.ም ይህ መመሪያ ከጸደቀበት ጊዜ ጀምሮ ሙሉ በሙሉ ተሸሮ በዚህ መመሪያ ተተክቷል፡፡

13. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

1/ ይህ መመሪያ የኢንስቲትዩቱ ስራ አመራር ቦርድ ጸድቆ ከሚያዚያ 2010 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተገለጸው ቢኖርም ይህ መመሪያ እንደገና አዲስ ቁጥር ከተሰጠበት ቀን በኋላ የሚነሳ መብት ወይም ግዴታ ህጋዊ ውጤት የሚኖረው መመሪያው በፍትህ ቢሮ ተመዝግቦ በአስተዳደር ተቋሙ ድረ-ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡